# አራራት

አራራት የኖኅ መርከብ ከጥፋት ውሃ በኋላ ያረፈበት የተራራ ስም ነው።

የሐመረ ኖኅ የሰንበት ት/ቤት የሥነ ጽሑፍ ክፍል ይህችን በየ3ወሩ አንድ ጊዜ እየታተመች የምትወጣ ጽሑፍ አራራት በማለት የሰየመውም በዚህ ምክንያት ነው።


እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ ፤ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት። በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት። ፩ኛ የጴጥ. ፭፥፮-፱

## ፍልሰታ ለማርያም

ፍልሰታ ማለት እንደ ዓረፍተ ነገሩ ትርጉሙ ይለዋወጣል፤

1. ፈለሰ ማለት ከቦታው ተነሣ፣ ለቀቀ፣ ጠፋ ማለት ይሆናል። ጉቶው ፈለሰ ሲባል ከሥሩ ከመሠረቱ ፈለሰ፣ ጠፋ ማለት ይሆናል፣

2. ከሃይማኖት ወደ ሃይማኖት መለዋወጥ መፍለስ ነው convert - መሆን መፍለስ የያዘውን ሃይማኖት ትቶ ወደ ሌላ እምነት መለወጥ ማለት ነው።

ስለዚህም ነው ፈላሻች እየተባሉ በሀገራችን የሚገኙ አይሁድ (ቤተ እስራኤል) የሚጠሩ ሁሉም መለወጥን፣ መለዋወጥን ያመለክታል፤ ቅድስት ማርያምን ፈለሰት ማርያም ይሏታል፣ ከነበረችበት ፈለሰች ወደማይታወቅ ዓለም ሄደች በማለት «ፈለሰት ማርያም»፤ «ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ» እየተባለ በብዙ ቦታ ይነገርላታል፣ ምክንያቱም ከዚህ ከግዙፉ ዓለም ወደ መንፈሳዊው ዓለም ተዛወረች፤ ከግዙፉ ዓለም ተለየች ለማለት በዚህ ቃል ይጠቀማሉ።

ቅድስት ማርያምን ፈለሰች የሚሉበት ምክንያቱ በ64 ዓመት ዕድሜዋ ሞታ ቅዱሳን ሐዋርያት ለመቅበር ሲወስዷት ከአይሁድ ወገን ምቀኞች አናሰቀብርም ብለው አስከሬኑን ለማቃጠል ቀምተው ሲወስዱ እጃቸውን መልአክ ቀጣቸው፤ ወዲያውም አስከሬኑ ተሰወራቸው፤ ሐዋርያት ስላልቀበሯት ፈለሰት ማርያም ብለዋል። ነገር ግን መላእክት አስከሬኑን ወስደው በገነት በዕፀ ገነት



ሥር አስቀምጠዋት ነበር፤ ከዚህ ዓለም ተለየች ከዚህ ዓለም ፈለሰች ለማለት ፈለሰት ማርያም እያሉ ስለተናገሩ ፍልሰታ ለማርያም፣ ፈለሰ ማርያም እየተባለ ይነገራል።

ይሁን እንጂ በመጨረሻው ጊዜ የቅድስት ማርያም አስከሬን ለቅዱሳን ሐዋርያት ተገልጦላቸው በጌቴ ሰማኒ ቀብረዋት በ፫ኛው ዕለት ተነሥታለች አሁንም አረገችና ሙስና መቃበር ሳታይ ስለቀረች ፈለሰት ማርያም የሚባለው ቃል ሲደጋገም ይገኛል።

ለቅድሰት ማርያም ታላላቅ ነገሮች ተሰርተውላታል፤ ስለዚህም ቅዱስ ገብርኤል «ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ» አላት፣ ይህም፥

ሀ- ወላጆቿ ከአረጁ ከአፈጁም በኋላ ለሴቶች የተሰጠው ግብር ከአለፈ በኋላ ሐና እና ኢያቄም ወለዷት፣ ይህም አምላካዊ ግብር ይባላል።

ለ- አምላክን በኅቱም ድንግልና ጸንሣ በኅቱም ድንግልና ወለደችው።

ሐ- አምላክን በድንግልና ጡቶቿ መገበችው

መ- የሚያቃጥል የሆነ አካለ መለኮትን በማሕጸኗ ወሰነችው።

ሠ- ዓለም የማይችለውን አምላክ በማሕጸኗ ቻለችው።

ስለዚህ ሁሉ በኋላ ስትሞት ሙስና መቃብር አላገኛትም፣ በክብር ወደ ሰማይ አረገች፣ ለሰው ልጅ የተዘጋጀውን ከዚህ ቀደም የሰው ልጅ ያላየውን ክብር ቅድስት ማርያም አየች፤ ለሰው ልጅ አሰቀድሞ የተዘጋጀውን መንግሥት ወረሰች። በዚህ ሁሉ ምክንያት ቅድስት ማርያም ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ሆና ስትመሰገን ትገኛለች።

እኛ ፍልሰታ እያልን በየዓመቱ 15 ቀን ነሐሴን የምናከብረው ይህንን ሁሉ ለመመስከር፣ በዚህ ሁሉ የተሰጣትን ክብር ለመለየትና ለማመስገን ነው።

ቅድስት ማርያም በተሰጣት ጸጋ ጸንታ በመኖሯ ለሰው ልጅ ሁሉ ሞገስን ሰጥታ ለሰው ልጅ ሁሉ መመኪያ ሆና ትኖራለች።

**አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ**

---

## ይህን ያውቁ ኖሯል?

ካለፈው የቀጠለ......

### ከይኩኖ አምላክ እስከ ዘመነ መሳፍንት

ከእነዚህ ቀጥሎ የተነሡት ዕውቅ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ነበሩ (1426 - 1460 ዓ.ም)። ዘመነ መንግሥታቸውም ወርቃማው የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ዘመን በመባል ይታወቃል። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ መንበረ መንግሥታቸውን ከተጉለት ወደ ደብረ ብርሃን አዛወሩ። በዘመነ መንግሥታቸው በጣም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ያሳነጹ፣ ብዙ መጻሕፍት የተጻፉበት ራሳቸው ብቻ 8 መጻሕፍት ጽፈዋል። ይህ ወቅት እንደ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የመሰሉ አባቶች የተነሡበት ነበር። አባ ጊዮርጊስ መጽሐፈ ምስጢር ን፤ አርጋኖን (ወደ ገጽ 3 ይዞራል)

### ከአራራት ዝግጅት ክፍል



እንኳን ለ፩ኛው ዓመት የአራራት ጋዜጣ ዝግጅት አደረሳችሁ አደረሰን!!!

«ጅማሬህ ታናሽ ቢሆንም እንኳ ፍጻሜህ እጅግ ይበዛል።»
መ. ኢዮብ ፰፥፯

## Touch me not; for I am not yet ascended to my Father

Some people have been asking why did Jesus say to Mary Magdalene, “Touch me not; for I am not yet ascended to my Father” but, allowed Thomas to do so. Different people have interpreted this verse variously. What does this verse really mean?

This verse is found in the Gospel according to St. John, chapter 20, verse 17. And its states, “Jesus saith unto her, Touch me not; for I am not yet ascended to my Father: But go to my brethren, and say unto them, I ascend unto my Father, and your Father; and to my God, and your God. Mary Magdalene came and told the disciples that she had seen the Lord, and that he had spoken these things unto her.”

So, why did John quote Jesus as having said, “Touch me not; for I am not yet ascended to my Father”? Should this be understood to mean that Mary Magdalene wasn’t allowed to touch Christ after His resurrection? To properly interpret this, it is important to realize that, as is frequently the case, John’s account offers a unique perspective on the event. His take offers more about what Christ sees in a person’s heart, rather than the synoptic accounts of sense perception. Compare John’s version with St. Matthew’s (28:9-10): “... Jesus met them, saying, All hail. And they came and held him by the feet, and worshipped him. Then said Jesus unto them, ‘Be not afraid: go tell my brethren that they go into Galilee, and there shall they see me.’”

St. John’s coverage of Christ’s initial appearance to St. Mary Magdalene might be better understood by reading the following paraphrase. Since you already believe that it is I, speaking to you, and that I have arisen, be assured that I will be around for a while, so that we may talk further. But, now, your assignment is to go and tell my brethren about my resurrection from the dead. Otherwise, this Bible citation is apt to be misinterpreted as meaning that she (a woman) should not touch Him after His resurrection and before His ascension. All the Gospels confirm Mary Magdalene to have been the first one to see Jesus after His resurrection. If the real issue had been that she wasn’t good enough to touch Him, Christ would have shown Himself to one or more of His disciples. It does not make sense to suppose women who discovered His resurrection before the rest of His followers; weren’t allowed to touch Him. Because Mary Magdalene had told the disciples the good news, she is known both as the apostle to the apostles, and as an equal to the apostles.

In another instance, Jesus invited Thomas to touch him. Thus, he, who had not been with the other disciples when Jesus appeared earlier, might realize our Lord knew what was in his heart, even while he yet doubted. In the same chapter, John reported “The other disciples, therefore; said unto him, ‘We have seen the Lord.’ But he said unto them, ‘Except I shall see in his hands the print of the nails, and put my finger into the print of the nails, and thrust my hand into his side, I will not believe.’ On the eighth day after the resurrection while the doors were shut, Jesus appeared again in the midst of His disciples and this time Thomas was in the house. Jesus said to them ‘Peace be unto you’”. Since there is nothing hidden from Our Lord Jesus Christ, He knew what Thomas had told the other disciples. And that is why after He greeted them said to Thomas, “Reach hither thy finger, and behold my hands; and reach hither thy hand, and thrust it into my side: and be not faithless, but believing (John 20:25). Reread the whole thing carefully. Note, this Gospel does not indicate whether or not Thomas touched our Lord. Instead, it records his faith statement, “My Lord and my God.”

Therefore, by comparing the above citations, we should learn that Christ desires all, including us, who have not seen what they saw, to receive the blessings of belief, rather than remaining faithless. We should appreciate Christ’s sensitivity to individual needs, in receiving the seed of faith, rather than gender differentiation, preferring that only men (the disciples) should touch Him after His resurrection.

Beide-Mariam Ejigu Retta

## አጫጭር ዜናዎች

በየዓመቱ የሚከበረው የትንሣኤ በዓል ዘንድሮም በደመቀ ሁኔታ ሚያዚያ ፲፩ ቀን (Apr 19, 2009) በመላው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ተከብሮ ውሏል።

ግንቦት ፩ (May 9, 2009) የግንቦት ልደታ ማርያም በዓል በሎስ አንጀለስ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ብዙ አባቶችና ምዕመናን በተገኙበት ተከብሮ ውሏል።

የካቴድራሉን ባዶ ቦታና የቦርድ ምርጫን በተመለከተ የተጠራው ስብሰባ በሰኔ 21 (June 28, 2009) ተከናውኗል።

በ፪ሺ፩ ዓ.ም. ትምህርታቸውን ከሁለተኛ ደረጃ ለአጠናቀቁ ወጣቶች ጸሎተ ቡራኬና ስጦታ ተበርክቶላቸዋል።

## ጠይቁን እንመልሳለን

*ይህ ዓምድ ከምዕመናን የሚጠየቁ ጥያቄዎችን የምናብራራበት፣ መልሰ የምንሰጥበት ነው።*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በተነሳ ጊዜ ማርያም መግደላዊትን ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ ብሎ ቶማስን ግን እንዲነካው ለምንድን ነው የፈቀደለት?

እህታችሁ ፀሐይ
ከኦክላንድ

የተለያየ ማብራሪያም ለዚህ ጥቅስ ተሰጥቷል። ለመሆኑ በትክክለኛው የዚህ ጥቅስ መልእክቱ ምንድን ነው?

በመሠረቱ ይህ ጥቅስ የሚገኘው በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20 ቁጥር 17 ላይ ነው፤ እንዲህም ይላል «ኢየሱስም። ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ። እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት። መግደለዊት ማርያም መጥታ ጌታን እንዳየች ይህንም እንዳላት ለደቀ መዛሙርቱ ነገረች። »

ዮሐንስ «ኢየሱስም ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ» ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ አጻጻፉ የሚመስለው መግደላዊት ማርያም ክርስቶስ ከተነሳ በኋላ እንዳትነካው የከለከላት ነው፤ ይሁን እንጂ ዮሐንስ ማመልከት የፈለገው ማርያም መግደላዊት በልቧ ያሰበችውን አውቆ ቅድሚያ ልታደርግ የሚገባውን ነገራት እንጂ በቀጥታ እንደተጻፈው መተርጎም የለበትም። ምክንያቱም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28፤9 ላይ ሴቶቹ (መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም) እንደነኩት በግልጽ እንዲህ ይላል፣ እነሆም

፥ ኢየሱስ አገኛቸውና። ደስ ይበላችሁ አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ አትፍሩ ፤ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ ፥ በዚያም ያዩኛል አላቸው።

ስለዚህ የዮሐንስ አባባል …«ከሞት መነሳ ቴንና የማነጋግርሽ እኔ እንደሆንኩ አምነ ሻል አሁንም ገና ስላላረግሁም እዚህ ምድር ላይ እቆያለሁም ለአንቺም በቂ ጊዜ አለ፤ ይልቅ ቶሎ አሁኑኑ ሂጂና ለወንድሞቼ ከሞት መነሳቴን ንገሪያቸው ለማለት ነው እንጂ ዐረፍተ ነገሩ ከተነሳ ሁ በኋላ ሴት አትነካኝም ለማለት አይ ደለም። በሁሉም ወንጌሎች ላይ ትንሣ ኤውን አስቀድሞ ያየችው ማርያም መግ ደላዊት እንደሆነች ተጽፏል። ሴቶች ለ መንካት በቂ ባይሆኑ ኖሮ አስቀድሞውኑ ከሐዋርያቱ ለአንዳቸው በተገለጸ ነበር። ስለዚህ ትንሣኤውን ከማንም በፊት ለማ የት ለታደሉ፤ መንካት አልተፈቀደላቸው ም ቢባል አያስኬድም። እንዲያውም ማርያም መግደላዊት የትንሣኤውን ዜና ሄዳ ለሐዋርያት በማብሰሯ፤ ሐዋርያ ለሐ ዋርያት ተብላለች።

በአንጻሩ ደግሞ ክርስቶስ ለምንድን ቶማ ስ እንዲነካው ፈቀደለት ለሚለው፤ በተነ ሳ ቀን ምሽት ላይ አስቀድሞ ለሌሎቹ በተገለጠ ጊዜ ቶማስ አብሯቸው አልነበ ረም። በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20ቁጥር 25 ላይ እንዲህ ይላል«ሌሎች ም ደቀ መዛሙርቱ ጌታን አይተነዋል ብለው ለቶማስ ሲነግሩት፤ እርሱ ግን የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ፣ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው።»

በተነሳም በስምንተኛው ቀን ሁሉም ሐዋ ርያት ቶማስንም ጨምሮ ተሰብስበው በዝግ ቤት ውስጥ ሳሉ በመሀከላቸው ተገልጾ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ከጌታችን ከእርሱ ምንም የተሰወረ ነገር ስለሌለ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቶማስ ያለውን ስለሚያውቅ በመሀከላቸው ተገ ልጾ ሰላም ለእናንተ ይሁን ካለ በኋላ፤ ቶማስን ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው ፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን ያለው። (ዮሐ. 20፤25)

እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ቶማስ ይን ካው አይንካው ግልጽ አድርጎ ይህ ዐረፍ ተ ነገር አያሳይም ነገር ግን ክርስቶስ በእርግጥ የተነሳው እሱ መሆኑን ቶማስ እንዲያምን፤ እንዲዳብሰው በፈቀደለት ጊዜ ቶማስ ማመኑን «ጌታዬ አምላኬ» ብሎ መናገሩም ነው።ጌታም ስላየኸኝ አምነሃል አለው እንጂ ስለነካኸኝ አላለ ውም።

ስለዚህ በዮሐንስ ወንጌል ላይ የተጻፈው ን አባባል መረዳት ያለብን ክርስቶስ እነ ዚያ ደቀመዛሙርት በሙሉ ልብ አምነ ውት እንዲከተሉት እንደሚፈልግ፤ እን ዲሁም እኛንም እነዚያ ሐዋርያቱ ያዩት ን ያላየነውን ደግሞ እንድናምን ፤ እምነ ተ ቢስ ሆነን እንዳንቀር ነው እንጂ፤ ክ ርስቶስን ከተነሳ በኋላ ለመንካት የተፈቀ ደላቸው ሐዋርያቱ (ወንዶች) ብቻ ናቸው ለማለት አይደለም።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን።

## <u>**ይህን ያውቁ ኖሯል**</u>? (ከገጽ 1 የዞረ)

ድንግልንና የሌሊት ጸሎት ሰዓታትን ጽ ፈዋል። በዚህ ወቅት ስለ ቅዱሳን፣ ስለ ቤተክርስቲያን ታሪክ ፣ ስለ አይሁድ ታ ሪክ፣ የተለያዩ መጻሕፍት ተተርጉመዋል ፤ ከእነዚህም አንዱ ተአምረ ማርያም ነው። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ሀገራቸውን አጠናክሮ ለመግዛት ዜጎቹን በአንድ እምነት ሥር ማምጣት እንዳለባቸው ስላ መኑና ክርስትና እንዲስፋፋ ካህናት እም ነትንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ለምእ መናን በሰንበትና በዐበይት በዓላት ቀን እንዲያስተምሩ ጥብቅ ትዕዛዝ አስተላል ፈው ነበር። ዓላማቸውንም ለማሳካት ይረዳቸው ዘንድ ከዚያ ቀደም ሆኖ የማ ያውቀውን በአንድ ጊዜ 3 ጳጳሳት ለማስ መጣት ችለው ነበር። በኢየሩሳሌም ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን አባቶች ለም ግብና ለልብስ መግዣ እንዲሆናቸው ከዘይላ ወደብ ከሚገኘው ቀረጥ በየሁለ ት ዓመቱ 100 ወቄት ወርቅ እንዲሁም ብዙ መጻሕፍትን ከሸኚ ደብዳቤ ጋር ልከውላቸዋል።

የመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችም የበለጠ እንዲስፋፋ ከፍ ያለ ጥረት አድርገዋል ። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ለክርስትና ሃይማኖ ት ፍጹም ቀናኢ ስለነበሩ ለጣዖት መስገ ድ የሞት ቅጣት እንደሚያስከትል ዐው ጀው፤ ይህን ሕግ ከመጣሳቸው የተነሣም ከተገደሉት መካከል የእሳቸው 8 ልጆቻ ቸው ይገኙበታል፤ ሁሉ ከሕግ በታች ነውና። በዚሁ በዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በ1441 በጣሊያን ፍሎረንስ በተካሄደው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ኢትዮጵያ እንድትገኝ ለቀረበላት ግብዣ በኢየሩሳሌም ከሚገኙት ኢትዮጵ ያውያን አባቶቻችን መካከል በገዳሙ አበምኔት አማካኝነት 2 ተወክለው ተገኝ ተዋል። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በመንፈሳዊ ውም ይሁን በሥጋዊው አስተዳደር ከፍ ተኛ ችሎታ ያሳዩ ታላቅ መሪ ናቸው።

ከእሳቸው በኋላ የነገሡት ልጃቸው በእ ደ ማርያም (1460-1470 ዓ.ም) ሲሆኑ የአባታቸውን ፈለግ በመከተል ብዙ አብ ያተ ክርስቲያናትን ያሳነጹና ብዙ መጻሕ ፍት እንዲጻፍ ያደረጉና ራሳቸው መልክ አ ሚካኤልንና መልክአ ቁርባንን ደርሰ ዋል። በተለይ በዘመኑ አትሮንሰ ማርያም የምትባለውን ቤተክርስቲያን አሠርተው፣ ውስጧን በወርቅና በዕንቊ አንቆጥቁጦ እንዳሠሯት በተጨማሪም በጣሊያኑ (ቬኒሺያኑ) ተወላጅ ብራንካ ሊዮን የም ስለ ፍቁር ወልዳን ሥዕል እንዲሣል አድርገዋል። እንዲሁም ከሳቸው ቀድ መው ያረፉትን የ22 ነገሥታት እንዲሁ ም በልጅነት የዳዊት መዝሙርን ያስተ ማራቸውን የመምህራቸውን የተክለ ኢየ ሱስን ዐፅም ከተቀበሩበት አስወጥተው በአትሮንሰ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እን ደገና እንዲያርፍ አድርገዋል።

## <u>ከቅዱሳት መጻሕፍት</u>

(ከማርያም ቅዳሴ የተወሰደ)

ወደ ቀደመው ነገር እንመለስ፤ ቅድስት ድንግልንም ለሁሉ ድንቅ የሚሆን የፅንሷ ን ነገር እንዲህ እያልን እንመርምራት። ድንግል ሆይ እሳተ መለኮት በሆድሽ ባደ ረ ጊዜ ፊቱ እሳት ልብሱ እሳት፤ ቀሚሱ እሳት ነው፤ እንደምን አላቃጠለሽ።

ሰባት የእሳት ነበልባል መጋረጃ በሆድሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ፤ ወዴትስ ተጋረደ፤ ከጐንሽ በቀኝ ነውን፤ ወይስ ከጐንሽ በግ ራ ነውን፤ ትንሽ አካል ስትሆኝ።

የሚያንጸባርቅ ነደ እሳት የሚከበው ኪሩ ቤል የተሸከሙት ዙፋን በሆድሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ፤ ወዴትስ ተተከለ፤ ታናሽ ሙሽራ ስትሆኝ።

ከገረድነት ጋራ እናትነት እንደምን ያለ ነው፤ ከስፋት ጋራ የሆድ መጥበብ፤ እን ደ ንብ ያለ ሩካቤ፤ ከቃል ድምፅ የተገኘ ፅንስ፤ ከድንግልና ጋራ አንድ የሆነ ሐሊብ።

ይህንም ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ የልጅሽን የባሕሩን ጥልቅነት ሊዋኝ ይወዳል የወዳ ጅሽ የመሠወሪያው ማዕበልም ያማታዋል።

ዳግመኛም ባሰብሁ ጊዜ ሕሊናዬ ተሠው ሮ ወደ ላይ ወጥቶ የሕያው መሠወሪያ የሆነውን ሊገልጥ ይወዳል። ከነደ እሳት

ነቱ የተነሣ ይፈራል ከዐየራት ከእርቧቸ ው አርቦ አይደርስም።
ይህንንም ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ በነፋስ ትከሻ ተጭኖ በምሥራቅና በምዕራብ በሰ ሜንና በደቡብ በዳርቻውም ሁሉ ሊበር ይወዳል። የፍጡራንን አኗኗር ያይ ዘንድ የአብሕርትንም ጥልቅነታቸውን ይለካ ዘንድ በሁሉ ዘንድ፤ በሁሉም ይዞራል። አቅቶት ወደ ቀደመ አኗኗሩ ይመለሳል።

አሁንም ገናንነቱን አንመርምር፤ ጥልቅነ ቱንም አንጠናቀቅ፤ የገናንነቱን መጠን ለማመስገን የነቢያትና የሐዋርያት አንደ በት የማይቻለው ነው።

የማይደፈር ግሩም ነው፤ በእኛ ዘንድ ግን ትሑት ነው። የማይገኝ ልዑል ነው በኛ ዘንድ ግን አርአያ ገብርን ነሣ። የማ ይዳሰስ እሳት ነው፤ እኛ ግን አየነው ዳሰስነውም፤ ከርሱም ጋራ በላን ጠጣን።

**The ANAPHORA OF ST. MARY**

Let us now return again to peak of the holy Virgin, speaking of her conception which is wonderful to all, and saying: O Virgin, when there abode in your womb the fire of the Godhead, Whose face is fire, Whose clothes are fire, Whose covering is fire, how did it not burn you?

In what part of your womb were the seven curtains of the flame of fire prepared and spread ? Were they in the right or the left side while you were such a small body?

In what part of your womb was the glittering cherubic throne, compassed by the flame of fire, prepared and planted while you were a young bride?

How wonderful it is! A mother and a maid; the narrowness of the womb and the infinite; conception without intercourse, as a bee conceives, from the voice of a word; milk (1) with virginity.

When I think of this, my mind likes to swim in the depth of your Son's seas, and the billows from the hiding-place of your Beloved sweep across it.

Again when I think of this my mind likes to soar and ascend secretly and draw back the curtains of the hiding-places of the Living One; it becomes afraid of the flame of fire and does not reach even one fourth of the way to heaven.



When I think of this my mind likes to mount the shoulders of the winds to fly east, west, north and south to all the ends (of the world) to see the nature of the creatures, to measure the depths of the seas and to know the height of heaven, and travelling thus to every part it becomes faint and returns again to its former place

Now let us not further enquire or even think of the greatness and profundity of Him Whose grandeur cannot worthily be praised, no, not by the tongues of the prophets nor of the apostles.

He is the mighty One Whom none can discern by subtle device_ but He became humble among us; He is the most high, to Whom none can attain_ but among us He took upon Him the form of a servant; He is the impalpable fire, but we saw Him and felt Him and ate and drank with Him.

## <u>መጪ ዝግጅቶች</u>

- የቅዱስ ገብርኤል በዓል በሲያትል፣ በሳን ሆዜ በሳን ዲያጎና በዲሲ ይከበራል።

- የፍልሰታ ጾም በነሐሴ ፩ (August 7) ይገባል። በየዕለቱ የጠዋትና የማታ ጸሎ ትና ትምህርት ይኖራል።

- የደብረ ታቦር በዓልን በደመቀ ሆኔታ ለማክበር የሐመረ ኖኅ ሰንበት ት/ቤት ለየት ያለ ዝግጅት ይዞ ለመቅረብ በዝግ ጅት ላይ ነው።

- መስከረም ፩ ፪፻፪ (Sept 11, 2009) የቅዱስ ዮሐንስና የዘመን መለወጫ ክብረ በዓል ይከበራል።

- በየዓመቱ የሚከበረው የመስቀል በዓል ዘንድሮም መስከረም ፲፯ (Sept 27, 2009) በደመቀ ሆኔታ በቤተ ክርስቲያናችን ግቢ ተከብሮ ይውላል።

አስተያየትና ጥያቄ ካላችሁ ወይም ደግሞ ጽሑፎቻቹህ እንዲወጣላችሁ የምትፈልጉ ካላችሁ በቤተ ክርስቲያኒቷ የአስተያየት መስጫ ያኑሩልን። ወይም ደግሞ በሚከተለው የሥነ ጽሑፍ ዝግጅት ክፍል ኢሜይል ይላኩልን። **hamere_noh@yahoo.com**

**<u>የቤተ ክርስቲያን መደበኛ አገልግሎቶች</u>**

ዘወትር እሁድ ጠዋት ከ7:00 - 12:00 የቅዳሴ፣ ስብከትና መዝሙር አገልግሎት ይካሄዳል።

ከ12:15 - 1:00 በሰንበት ት/ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የመዝሙር መርሐ ግብር ይካሄዳል።

ዘወትር ረቡዕ እና ዓርብ ማታ ከ6:00 - 8:00 የሠርክ ጸሎትና የመጸሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይካሄዳል።

ለተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት፤ የሠርግ፣ የክርስትና፣ የፍትሐት አገልግሎትን ለምትሹ በ 510 336 1168 ደውለው ያነጋግሩን።